# እንኳን ደህና መጣችሁ

# የታክስ ከፋይ ምዝገባ፣ ስረዛ እና ክሊራንስ አሰጣጥ




ሚይዝያ/2018 ዓ.ም




## ክፍል አንድ:- አጠቃላይ ሁኔታ

1.1. ዓላማ

1.2. ወሰን

1.3. ትርጓሜ

## ክፍል ሁለት:- ለታክስ ከፋይነት ስለመመዝገብ

2.1. ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች

2.2 ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ




2.3. የምዝገባ ቦታ

2.4. የታክስ ከፋይ ምዝገባ ልዩ ሁኔታዎች

2.5. ምዝገባን ስለመሰረዝ

ክፍል ሶስት:- ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ

3.1. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ስለመሰጠት

3.2. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም

3.3. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥርን ስለመሰረዝ




ክፍል አራት፡- ለውጦችን ስለማሳወቅ

4.1. ታክስ ከፋዩ የሚያሳውቃቸው ለውጦች

4.2. የለውጥ ማሳወቂያ ቅጽ

ክፍል አምስት፡- የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

5.1. የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው

5.2. የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች




5.3. ክሊራንስ ለመስጠት ኦዲት የማያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

5.4. የታክስ ክሊራንስ ከመሰጠቱ በፊት ኦዲት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

5.5. የታክስ እዳ ስለመኖሩ ማጣራት እና የታክስ ስሌት የሚያስፈልጓቸው አገልግሎቶች

5.6. የአገልግሎት አዲት ወይም የአጠቃላይ ኦዲት ወይም የታክስ ስሌት ግኝት መሠረት በማድረግ ስለሚሰጥ ውሳኔ

5.7. የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የሚያገለግልበት ጊዜ




5.8. የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት መስጠት

ክፍል ስድስት:- አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች

6.1. አስተዳደራዊ ቅጣቶች

6.2. የወንጀል ተጠያቂነት

ማጠቃለያ

ማጣቀሻ

# 1.1. ዓላማ

## ❑ ዋና ዓላማ

በታክስ አስተዳደር ህግ መሰረት በመወያየት ስለ ምዝገባ፤ለውጦችን ስለማሳወቅ፤ክሊራንስ እና ስለ ስረዛ ይገልጻሉ

## ❑ ዝርዝር ዓላማ

➢ ስለታክስ ከፋይ ምዝገባ፤ ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ አጠቃቀም እና ስረዛን፤የምዝገባ ቦታ፤ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የሚያገለግልበት ጊዜ እንዲሁም ስለክሊራንስ ያሉ ዋና ዋና ቃላት ትርጉም ይገልጻሉ፤

## ዝርዝር ዓላማ...

- ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው እንዲሁም የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ለማግኘት ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ይዘረዝራሉ፤
- የታክስ ከፋይ ምዝገባ የሚከናወንበትን የምዝገባ ቦታ ይገልጻሉ፤
- ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩን ከምዝገባ የሚሰርዝባቸው ምክንያቶችን ያብራራሉ፤
- ባለሥልጣኑ ምን ምን ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ሊሠረዝ እንደሚችል ይለያሉ፤

# ዝርዝር ዓላማ…

- ግብር ከፋዩ ከሚያከናውነው የንግድ እንቅስቃሴ ጋር የሚያደርጋቸውን ለውጦች ለግብር ባለሥልጣኑ ስለሚያሳውቅበት ሁኔታ ይገልጻሉ፤

- ከታክስ ምዝገባ፣ ስረዛ፣ ለውጥን ከማስታወቅ እና የታክስ ክሊራንስ ጋር ተያይዞ የግብር ከፋይ ግዴታዎች ህጋዊ ውጤት ይገልጻሉ።



# 1.2. ወሰን




- የሰነዱ ሽፋን
- የሥልጠና ተሳታፊዎች
- ግብር ከፋዩና በግብር ከፋዩ ድርጅት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች የስልጠናው ተሳታዎች ሲሆኑ እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች ግለሰቦችን እና ድርጅቶች ይጨምራል።
- ጊዜ



- የታክስ ከፋይ ምዝገባ
- የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር
- ተቀጽላ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር
- የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ
- የማንነት አካላዊ መረጃ
- የንግድ ማህበር
- ለውጥ
- የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት






# ክፍል ሁለት

## ለታክስ ከፋይነት ስለመመዝገብ .3



## 2.1. ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለባቸው ሰዎች

- አስቀድሞ የተመዘገበ ካልሆነ በስተቀር በታክስ ሕግ መሠረት ታክስ የመክፈል ኃላፊነት ያለበት ሰው በባለሥልጣኑ ዘንድ ለመመዝገብ ማመልከት አለበት፡፡
- በሰኘጠረዥ “መ” መሰረት ገቢ ያገኘን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ግለሰብ ወይም ድርጅትን እና አጠቃላይ ከሰንጠረዥ “መ” ጋር በተያያዘ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ብቻ ያለው ግለሰብ ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

# ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ...

- በንግድ ወይም በሙያ ሥራ (መቀጠርን ሳይጨምር)
- ቤት ማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ
- ተቀጣሪ
- የመንግገስት የልማት ድርጅት
- የመንግስት ባለበጀት መስሪያ ቤት
- መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
- የሃይማኖት ተቋማት

# ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ...

- በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ኩባንያ በቋሚነት የሚሰራ ድርጅት
- የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች
- በጋራ ሃብትነት ያልተመዘገበ ሃብት ያላቸው ሰዎች
- ባለ ልዩ መብት
- በመንግስታት መካከል የሚደረግ ስምምነት/በጽ/ቤት ማቋቋያ ስምምነት የሚቋቋም ድርጅት
- የኩባንያ አክሲዮን ባለድርሻ

## ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ...

- ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚያመለክት በሚሆንበት ጊዜ የሚጠየቀው የማንነት መለያ በተቀጣሪው መቅረብ ይኖርበታል። ቀጣሪው እንዲመዘገብ ያላደረገው ተቀጣሪ ካለበት የመመዝገብ ግዴታ ነጻ ሊያወጣው አይችልም።

- ሥራውን ከመጀመሩ ወይም ገቢ ከማግኘቱ በፊት ለታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ የምዝገባ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት።

# ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ…

- ለምዝገባው የሚቀርበው ማመልከቻ:- ባለሥልጣኑ ባጸደቀው ቅጽ መሠረት፣ የጣት አሻራ መለያን ጨምሮ የግለሰቡን ማንነት ከሚያረጋግጥ የሰነድ ማስረጃ የታክስ ከፋዩ ለታክስ የመመዝገብ ግዴታ ካለበት ቀን አንስቶ በ21 ቀናት ውስጥ ወይም ባለሥልጣኑ በፈቀደው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።
- ባለሥልጣኑ ለመመዝገብ ማመልከቻ ያቀረበውን ሰው ጥያቄ ያልተቀበለው ከሆነ የምዝገባውን ጥያቄ የማይቀበለው መሆኑን ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ባሉት 14 (አስራ አራት) ቀናት ውስጥ ለምዝገባ ላመለከተው ሰው በጽሑፍ ያሳውቀዋል።

## 2.2 ለታክስ ከፋይነት የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

❑ በምዝገባ ወቅት በሁሉም ተመዝጋቢዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑ ተግባራት

- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በሚገባ የተሞላውን ቅጽ መሙላት
- ወቅታዊ ወይም የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ/ፓስፖርት/የታደሰ መንጃ ፍቃድ፤
- ከ6 ወር ወዲህ የተነሳ ጉርድ ፎቶግራፍ፤



# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

- ❑ በንግድ ወይም በሙያ ሥራ (መቀጠርን ሳይጨምር) የተሠማራ ወይም ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ እንዲሁም ተቀጣሪ በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ሲቀርብ፡-

የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ ማቅረብና የማንነት አካላዊ መረጃ መስጠት፤ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር ፓስፖርት ወይም የግለሰቡን የግል መረጃ የያዘ ጉርድ ፎቶግራፍ የተለጠፈበት ወቅታዊ የኢትዮጵያ ወይም የሌላ ሀገር የታደሰ መንጃ ፍቃድ፤

# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

❑ የንግድ ማህበር በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በሚቀርብበት ጊዜ:-

- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በሚገባ የተሞላውን የማመልከቻ ቅጽ፤
- በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የማህበር መመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ፤
- የድርጅቱ ጽ/ቤት (የሥራ ቦታ) በማህበሩ ባለቤትነት ሥር ያለ ከሆነ የባለቤትነት ማረጋገጫ ወይም የኪራይ ከሆነ በውልና ማስረጃ የፀደቀ ውል፤
- አመልካቹ ወኪል ከሆነ ስለውክልናው የተሰጠውን ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ ወይም በምስረታ ላይ ያለ ማህበር ወኪል ለመሆን በሁሉም አባላት ፊርማ የተረጋገጠ ውክልና፤

# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

## የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ሲቀርቡ

- ድርጅቱ የተቋቋመበት ሕግ፤
- የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፤
- የድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ከስድስት ወር ወዲህ የተነሳው ጉርድ ፎቶግራፍ እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር፤
- አመልካቹ ወኪል ከሆነ ስለውክልናው የተሰጠውን ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ።

# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

## ❑የመንግሥት ባለበጀት መ/ቤት በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ሲቀርብ፡-

- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በሚገባ የተሞላውን ቅጽ፤
- የመ/ቤቱን ማቋቋሚያ ሕግ፤
- መ/ቤቱን የሚወክለው ሰው የውክልና ደብዳቤና የግለሰቡ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ አለባቸው።

# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

❑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ሲቀርቡ፦

- በባሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በአግባቡ የተሞላውን ቅጽ፤
- በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የፀደቀ የመመስረቻ ጽሑፍና መተዳደሪያ ደንብ፤
- የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፤
- የስራአስኪያጁ ወቅታዊ የማንነት መግለጫ

# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

የሃይማኖት ተቋማት በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ሲቀርቡ:-

- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በአግባቡ የተሞላውን ቅጽ፤
- አግባብ ባለው የመንግሥት አካል የተሰጠ የምዝገባ የምስክር ወረቀት፤
- የሃይማኖት ተቋሙን የሚወክለው ሰው ሕጋዊ የውክልና ማስረጃ፤
- የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም ተወካይ የማንነት መገለጫ

# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

- በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ኩባንያ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ሲቀርብ:-

- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በአግባቡ የተሞላውን ቅጽ፤
- በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ኩባንያ በውጪ ሀገር የተመሠረተበትን የምስክር ወረቀት፤
- በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ኩባንያ በቋሚነት የሚሠራ ድርጅት የሚሠራበትን ቦታ  አድራሻ የሚገልጽ ሰነድ፤
- የድርጅቱ ዋና ስራአስኪያጅ የማንነት መገለጫ

# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

- የፌደራል መንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የወጪ መጋራት ተጠቃሚዎች (ተማሪዎች) ለመመዝገብ ሲቀርቡ:-

- በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውንና በአግባቡ የተሞላውን ቅጽ፤
- የማንነት አካላዊ መረጃ መስጠት፤
- በሚማርበት ዩኒቨርስቲ የታደሰ መታወቂያ ካርድ ማቅረብ አለባቸው።

# የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

- በጋራ ሀብትነት ያልተመዘገበ ሀብት ያላቸው ሰዎች እንዲሁም ባለ ልዩ መብቶች በታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ሲቀርቡ፡-

- የጋራ ሀብቱ ባለቤቶች በውክልና ማስረጃ የተረጋገጠ ሙሉ ውክልና የሰጡበት የሰነድ ማስረጃ፤
- ባለልዩ መብት ልዩ መብት ያለው ስለመሆኑ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የተረጋገጠ የሰነድ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
- የግለሰብ የማንነት መግለጫ

## የመመዝገብ ግዴታ ያለበት ሰው ማሟላት ያለበት ቅድመ ሁኔታ

- ❑ በመንግሥታት መካከል በሚደረግ ስምምነት ወይም በጽ/ቤት ማቋቋሚያ ስምምነት የተቋቋሙ ድርጅቶች ለምዝገባ በሚቀርቡበት ጊዜ

- ➢ ድርጅቱ ወይም ጽ/ቤቱ የተቋቋመበት ስምምነት፤
- ➢ ድርጅቱ ወይም የጽ/ቤቱ ሥራ አስኪያጅ የምደባ ደብዳቤ፤
- ➢ የስራአስኪያጁ የማንነት መገለጫ

# ሙከራ አንድ

- አንድ ሰው ለታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ ምን ምን ቅድመ-ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት?

# 2.3. የምዝገባ ቦታ

- ታክስ ከፋዩ ነዋሪ በሆነበት ወይም የንግድ ሥራውን በሚያከናውንበት ስፋራ ባለው የታክስ ቅርንጫፍ ነው፡፡
- በባለሥልጣኑ በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት ያለው ድርጅት በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ያለበት ዋና መሥሪያ ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ ቅ/ጽ/ቤት ይሆናል፡፡
- ከአንድ በላይ በሆነ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ውስጥ በንግድ ሥራ የተሠማራ ወይም ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ ወይም ድርጅት ገቢውን ባገኘበት መመዝገብ አለበት፡፡

# ቦታ…

- በአንድ ክልል ወይም ከተማ አስተዳደር ውስጥ በተለያየ ቦታ የንግድ ሥራ የሚያካሄድ ወይም ቤት በማከራየት ገቢ የሚያገኝ ግለሰብ በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ያለበት ዋና መሥሪያ ቤቱ በሚገኝበት ቦታ ባለው ቅ/ጽ/ቤት ይሆናል።
- ታክስ ከፋይ በተለያዩ ክልሎች ወይም ከተማ አስተዳደሮች ውስጥ በአንድ ወይም በተለያዩ የንግድ ዘርፎች ላይ የተሠማራ ከሆነ በምዝገባ ማመልከቻ ቅፅ ላይ የሁሉንም አድራሻ እና የንግድ ዓይነት ዝርዝር መሙላት አለበት።



# 2.4. የታክስ ከፋይ ምዝገባ ልዩ ሁኔታዎች

- አመልካቹ ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሞግዚት በሚሆንበት ጊዜ፤ ልዩ የማንነት አካላዊ መረጃ እንዲሰጥ በማድረግ በስሙ የሚመዘገብ ይሆናል፡፡
- በሞግዚትነት የሚተዳደር ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ሰው የማንነት አካላዊ መረጃ በመስጠት በስሙ የሚመዘገብ ቢሆንም የማስተዳደር ኃላፊነቱ ግን የሞግዚቱ ይሆናል፡፡
- መመዝገብ ሲኖርበት ያልተመዘገበን ሰው ባለሥልጣኑ ሊመዘግብ የሚችል ሲሆን በ10 ቀናት ውስጥ ታክስ ከፋዩ በአካል ቀርቦ እንዲመዘገብ በደብዳቤ ጥሪ ሊያደርግለት ይችላል፡፡

# የምዝገባ ልዩ ሁኔታዎች...

- ባለሥልጣኑ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሊመዘገብ ይችላል፡፡
- በሠንጠረዥ "መ" መሠረት የመጨረሻ ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ታክስ ከፋይ ይህንን ገቢ በሚመለከት በታክስ ከፋይነት ሊመዘገብ አይችልም፡፡
- በውጪ ሀገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያለው ሰው ለታክስ ከፋይነት ለመመዝገብ በአካባቢው በሚገኝ የኢትዮጵያ ኢምባሲ ወይም ቆንስላ በአካል በመገኘት የማንነት አካላዊ መረጃ መስጠት ይችላል፡፡

## ሙከራ ሁለት

1. የታክስ ከፋይ ምዝገባ የሚከናወንበትን የምዝገባ ቦታ ግለጹ?
2. በታክስ ምዝገባ በልዩ ሁኔታዎች የሚስተናገዱትን እነማን ናቸሰው?

# 2.5. ምዝገባን ስለመሰረዝ

- የመመዝገብ ግዴታ ሲቋረጥ ምዝገባው እንዲሰረዝለት ለባለሥልጣኑ የሚያመለክት ሲሆን በ30 ቀናት/ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት።
- ባለሥልጣኑም በ90 ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ኦዲት ሊያደርግ ይችላል።
- የአንድ ሰው ምዝገባ መሰረዝ በሌላ ታክስ ሕግ ለአንድ የተለየ ታክስ ዓላማ ሲባል የተደረገ ምዝገባ መሰረዝንም ይጨምራል።

# ስለመሰረዝ…

- አንድ ሰው ምዝገባ እንዲሰረዝለት ጥያቄ ካላቀረበ ባለሥልጣኑ ይህ ሰው ሥራውን ሙሉ በሙሉ ማቆሙን እና ለታክስ ሕጎች ዓላማ የመመዝገብ ግዴታ የሌለበት መሆኑን እንዲሁም የተፈጥሮ ሰው ከሆነ መሞቱን፣ ኩባንያ ከሆነም መፍረሱን ወይም ሌላ ማንኛውም ሰው ሕልውናው የተቋረጠ መሆኑን ሲያምንበት ለታክስ ከፋዩ ወይም ለታክስ እንደራሴው የጽሑፍ ማስታወቂያ በመስጠት ምዝገባውን ይሰርዛል።



# ሙከራ አራት

- ባለሥልጣኑ ታክስ ከፋዩን ከምዝገባ የሚሰርዝባቸው ምክንያቶችን አብራራ/ሪ?

# 3.1. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ስለመሰጠት

- አንድ ታክስ ከፋይ ከአንድ መለያ ቁጥር በላይ ሊኖረው አይችልም። ከ1 በላይ በሆኑ ክልሎች/የከተማ አስተዳደር በንግድ ሥራ/ቤት በማከራየት ሥራ ላይ ተሠማርቶ ገቢ የሚያገኝ ሰው ተቀጽላ ያለው መለያ ቁጥር ሊሰጠው ይችላል።
- መለያ ቁጥር በመያዝ ብቻ የታክስ ግዴታ እንዲወጣ አይጠየቅም።
- መለያ ቁጥሩ በተለያዩ ምክንያቶች ከተበላሸና በጽሑፍ ካመለከተ የተበላሸውን መልሶ ነባሩን መለያ ቁጥር የያዘ የምስክር ወረቀት ታትሞ ይሰጠዋል።

## 3.2. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አጠቃቀም




- መለያ ቁጥር በታክስ ሕግ መሠረት በሚዘጋጅ ሰነድ ላይ መገለጽ ይኖርበታል፤
- ታክስ ከፋዩ ታክስ ቀንሶ የማስቀረት ግዴታ ላለበት ሰው ክፍያዎች በሚፈጽምበት ጊዜ መለያ ቁጥሩን ማሣወቅ አለበት።
- የንግድ ሥራ ለመሥራት ፈቃድ ይሰጠው ዘንድ ማመልከቻ የሚያቀርብ ታክስ ከፋይ ፈቃድ ለሚሰጠው ባለሥልጣን የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን መስጠት አለበት።

## መለያ ቁጥር አጠቃቀም...

- የንግድ/የሥራ ፈቃድ የሚሰጥ የመንግሥት አካል/ተቋም ታክስ ከፋዩ መለያ ቁጥሩን ሳያቀርብ ፈቃድ መስጠት አይችልም።
- ፈቃዱን በሚያድስበት ጊዜ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ማቅረብ የሚጠበቅበት የመጀመሪያው የፈቃድ ማመልከቻ ከቀረበ ወዲህ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩ የተቀየረ እንደሆነ ብቻ ነው።
- መለያ ቁጥር ለተሰጠው ሰው ብቻ የሚያገለግል ስለሆነ ከታክስ ወኪል በሌላ ሰው ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም።

# 3.3. የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥርን ስለመሰረዝ

- እውነተኛ ባልሆነ ማንነት መለያ ቁጥሩ ከተሰጠ፤
- ታክስ ከፋዩ ከአንድ በላይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ከያዘ፤
- ታክስ ከፋዩ ማንኛውንም ገቢ የሚያገኝበትን ሥራ ሲያቆም።

# ሙከራ አራት

- ባለሥልጣኑ ምን ምን ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በመስጠት የአንድን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ

ቁጥር ሊሠረዝ ይችላል

# 4.1. ታክስ ከፋዩ የሚያሳውቃቸው ለውጦች



- በንግድ ድርጅቱ ስያሜና በአክሲዮን ባለድርሻ አባላት ላይ

- በድርጅቱ ስም የተመዘገበ አድራሻ ለውጥ፤

- በዋነኛ የሥራ እንቅስቃሴው/በቅርንጫፍ/በንግድ ሥራው
  መተዳደሪያ ደንብ/የመመስረቻ ጽሑፍ/የሽርክና ስምምነት ላይ የተደረገ ለውጥ፤

- የንግድ ሥራውን በከፊል/በሙሉ በማቋረጥ ወይም በሽያጭ/በስጦታ በማስተላለፍ/በመለወጥ/በዋስትና በማስያዝ በድርጅቱ ላይ የተደረጉ ለውጦች፤

## ስለማሳወቅ...

- በንግድ ሥራ ወኪል/የታክስ እንደራሴ ላይ የተደረገ ለውጥ፤
- የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ለካፒታል ማሳደጊያ ሲውል፤
- የገቢ ምንጭ መቋረጡን ወይም መሻሻልን በተመለከተ፤
- የታክስ ከፋዩ ሠራተኛ ሲጨምር/ሲቀንስ ወይም የሠራተኞች የደመወዝ ለውጥ ሲያደርግ፤



# 4.2. የለውጥ ማሳወቂያ ቅጽ

- **ሚኒስቴሩ፤** ያዘጋጀውን ቅጽ እንደ አስፈላጊነቱ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለታክስ ከፋዮች ተደራሽ እንዲሆን ያደርጋል፤ ይቀበላል፡፡

- **ግብር ከፋዩ፡-** የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ታክስ ለሚከፍልበት ቅ/ጽ/ቤት ለውጡ በተደረገ በ30 ቀናት ውስጥ ማቅረብ አለበት፤

- የታክስ ከፋይ ለውጥ የሚያሳውቅበትን ቅጽ የሚቀርብ የለውጥ ማስታወቂያ የ3ኛ ወገን ማረጋገጫ የሚያስፈልገው ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ ማረጋገጫ ከተሞላው ቅጽ ጋር በማያያዝ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

# ሙከራ አምስት

- ታክስ ከፋይ ምን ምን ዓይነት ለውጦችን ሲያደርግ ነው ለሚኒስቴሩ በጽሑፍ ማሳወቅ ያለበት

# ክፍል አምስት

# የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ

## 5.1.የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የአገልግሎት ዓይነቶች




- የንግድ ሥራ ፍቃድ/የሙያ ፍቃድ ለማደስ ወይም ለመመለስ፤ የባንክ ብድር ለማግኘት፤
- በጨረታ ለመካፈል ወይም ለመሳተፍ፤
- የተሽከርካሪዎች ወይም የኮንስትራክሽን ማሽነሪ ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ (ክላውዶ) ለማድረግ፤
- ለተሽከርካሪ የመድን ካሳ ለማግኘትና የስሌዳ ለውጥ ለማድረግ፤

# ምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የአገልግሎት ዓይነቶች…

- የድርጅት ስም ወይም አድራሻ ለመለወጥ፤
- ጥቅም የሚከፈልበት የካፒታል ሃብት ለማስተላለፍ፤
- ድርጅት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ለመዝጋት ወይም ዘርፍ ለመቀየር፤
- የባለቤትነት ስም ምዝገባ የሚያስፈልገውን የንግድ ሥራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፤
- ሕጋዊ ህልውና የነበራቸው ድርጅቶች በአንድ ላይ ለማደራጀት ወይም ለማዋሀድ፤

# ምስክር ወረቀት የሚሰጥባቸው የአገልግሎት ዓይነቶች...

- የንግድ መደብር ለሌላ አካል በሽያጭ፣ በስጦታ፣ በውርስ ወይም በመሳሰሉት ለማስተላፍ፤
- ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ስለመከፈሉ ለተቀጣሪው የሚሰጥ ማረጋገጫ፤
- የከፍተኛ ትምህርት ውጪ መጋራት ተጠቃሚ በትምህርት ዘመኑ የተጋራውን ወጪ በአገልግሎት ወይም በክፍያ ስለመወጣቱ የሚሰጥ ማረጋገጫ፤ሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች ለማግኘት።

## 5.2. የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አገልግሎት ለማግኘት መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

- እንዲሰጠው በጽሑፍ ጥያቄ ማቅረብ፤
- ውዝፍ የታክስ ዕዳ /ወቅታዊ የታክስ ክፍያ የፈጸመ ወይም ለመክፈል የክፍያ ስምምነት የገባና በውሉ መሠረት እየተከፈለ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ፤
- በደረሰው የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ላይ ቅሬታ ያለው ታክስ ከፋይ በታክስ ውሳኔ ቅሬታ አጣሪ ክፍል ወይም ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ወይም በየደረጃው ለሚገኝ ፍርድ ቤት ቅሬታውን አቅርቦ በመታየት ላይ የሚገኝ ስለመሆኑ የጽሑፍ ማስረጃ ማቅረብ አለበት።

## መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች...

- ታክስ ከፋዩ የታክስ ነጻ መብት ያለው ወይም በግብር እፎይታ ጊዜ ላይ ያለ ስለመሆኑ የጽሑፍ ማስረጃ፤
- በግብር ዓመቱ በታክስ ከፋይነት ያልተመዘገበ ከሆነ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አለመውሰዱ እና የታክስ ፋይል በስሙ አለመከፈቱ አስኪረጋገጥ፤
- በንግድ ሥራ ፍቃዱ ምንም ዓይነት ሥራ አለመሥራቱን የገለጸ ታክስ ከፋይ አለመሥራቱ እስኪረጋገጥ፤

# ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች…

- በኮንስትራክሽን ማሽነሪ ማከራየት ዘርፍ የተሠማራ ታክስ ከፋይ ፣ በታክስ ጊዜው ታክስ ያልከፈለው ማሽነሪው በመበላሸቱ ምክንያት መሆኑንና ይህንኑ በታክስ ሕጉ መሠረት ማስታወቁን እና ለዚሁም በ3ኛ ወገን የተረጋገጠ ማስረጃ እስኪያቀርብ፤
- ታክስ ከፋዩ ቦሎ ለማደስ የኮንስትራክሽን ማሽን በመበላሸቱ ምክንያት ያለመሥራቱን በ30 ቀናት ውስጥ ማስታወቁ እስኪረጋገጥ፤
- የኮንስትራንሽን ማሽነሪ ለመሸጥ ከሆነ ማሽነሪው ከቆየበት ቦታ (ጋራዥ) ወይም ከቆመበት ቀበሌ አስተዳደር ማረጋገጫ ማስረጃ እስኪያቀርብና እስኪረጋገጥ፤

# ማሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች...

- በታክስ ጊዜው ታክስ ያልከፈለው የተሽከርካሪው ሊብሬ እና ታርጋ ለመንገድ ትራንስፖርት በመመለሱ/መድን ድርጅት ቅሪት አካልን በመረከቡ ምክንያት ስለመሆኑ ማስረጃ እስኪያቀርብ፤
- የወጪ መጋራት አገልግሎት/ክፍያ ተጠቃሎ እስኪፈጽም ድረስ፤
- ከታክስ ከፋዩ የሚፈልገው ታክስ የሚሰበሰብ ስለመሆኑ ስጋት ሲኖረውና ታክሱ በአስቸኳይ መሰብሰብ ያለበት ሆኖ ሲገኝ ታክሱ ሳይሰበሰብ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አይሰጥም



# ሙከራ ስድስት

- አንድ ግብር ከፋይ የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት ለማግኘት ምን ምን ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት ይጠበቅበታል?

## 5.3. ክሊራንስ ለመስጠት አዲት የማያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

- ❑ ንግድ ሥራ ፍቃድ ወይም የሙያ ፍቃድ ለማደስ፤
- ❑ ጨረታ ለመካፈል/ለመሳተፍ፤ እና የባንክ ብድር ለማግኘት፤
- ❑ ለተሽከርካሪዎች/ለኮንስትራክሽን ማሽነሪዎች ዓመታዊ ምዝገባና ምርመራ (ክላውዶ) ለማድረግ፤
- ❑ የመድን ካሳ ለማግኘትና የተሽከርካሪ ሰሌዳ ለውጥ ለማድረግ፤
- ❑ የድርጅት ስም ወይም አድራሻ ለመለወጥ፤ እንዲሁም የንግድ ሥራ ሀብት መቀነስን ሳይጨምር የንግድ ዘርፍ ቅነሳ ለማድረግ፤
- ❑ ድርጅቶች እንደገና ተደራጅተው ሲዋሀዱ የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳ አካቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የፀደቀ ሰነድ ሲቅረብ፤

## 5.4. የታክስ ክሊራንስ ከመሰጠቱ በፊት ኦዲት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

- የሚሸጠው ወይም የሚተላለፈው የንግድ ሥራ ሀብት ከሃምሳ በመቶ ያነሰ ከሆነ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት አገልግሎት ኦዲት ሥራ መከናወን አለበት።

- በከፍተኛ እና መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የሚስተናገድ ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ መካከለኛ እና ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ ከታች ላሉት አገልግሎቶች የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት አገልግሎት ኦዲት መደረግ አለበት።

# ኦዲት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

- ከሃምሳ በመቶ በላይ የንግድ ሥራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፣
- ድርጅትን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመዝጋት፣
- የንግድ ዘርፍ ለመቀየር ወይም ለመቀነስ ከሆነ፡፡

❑ በከፍተኛ እና በመካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የሚስተናገድ ታክስ ከፋይ በግብር ዘመኑ በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ ከሆነ በሚከተሉት አገልግሎቶች ላይ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት አጠቃላይ ኦዲት መደረግ አለበት፣

# አዲት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

- ከሃምሳ በመቶ በላይ የንግድ ሥራ ሀብት ለመሸጥ ወይም ለማስተላለፍ፣
- ድርጅትን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለመዝጋት፣
- የንግድ ዘርፍ መቀየር ወይም መቀነስ ከሆነ፣
- ድርጅቶች በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሀድ በውህደት የሚፈጠረው ድርጅት የተዋሀደውን ድርጅት የታክስ ዕዳን ለመክፈል ግዴታ ገብቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ ሰነድ ከቀረበ፣
- የንግድ መደብሩን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በውርስ ለማስተላለፍ፣

# ኦዲት የሚያስፈልጋቸው አገልግሎቶች

- በየትኛውም የስጋት ደረጃ ላይ የሚገኝ የአነስተኛ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ታክስ ከፋይ ከሀምሳ በመቶ በላይ የሆነውን የንግድ ሥራ ሀብቱን ወይም የንግድ መደብሩን ለሶስተኛ ወገን በሽያጭ፣ በስጦታ ወይም በውርስ ለማስተላለፍ ወይም የንግድ ሥራውን ለማቋረጥ የክሊራንስ የምስክር ወረቀት ጥያቄ በሚያቀርብበት ጊዜ አጠቃላይ ኦዲት ተከናውኖ ዕዳ የሌለበት መሆኑ ሲረጋገጥ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀቱ ይሰጠዋል፡፡

## 5.5. የታክስ እዳ ስለመኖሩ ማጣራት እና የታክስ ስሌት የሚያስፈልጓቸው አገልግሎቶች

- ጥቅም የሚከፈልበት የካፒታል ሃብት ማስተላለፍ፤
- ድርጅት በአንድ ላይ ለመደራጀት ወይም ለመዋሃድ በውህደት የሚፈጠረው ድርጅት የተዋሃደውን ድርጅት የታክስ እዳ ለመክፈል ግዴታ ገብቶ የሚዋሃዱ ስለመሆኑ የሚያስረዳ እና የቴምብር ቀረጥ የተከፈለበት ውል ከቀረበ፤
- የከፍተኛ ትምህርት የወጪ መጋራት ግዴታን ስለ መወጣት ማስረጃ ሲጠየቅ፤
- ከመቀጠር የሚገኝ ስራ ላይ ግብር ስለመከፈሉ።

## 5.6. የአገልግሎት አዲት ወይም የአጠቃላይ ኦዲት ወይም የታክስ ስሌት ግኝት መሠረት በማድረግ ስለሚሰጥ ውሳኔ

ማንኛውም ታክስ ከፋይ በታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሊከፈል የሚገባው የታክስ እዳ ያለበት መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ እዳውን ሳይከፍል ወይም የክፍያ ስምምነት ሳይገባ ወይም የባንክ ዋስትና ሳያሲዝ የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አይሰጠውም፡፡

## 5.7. የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት የሚያገለግልበት ጊዜ

- በጨረታ ለመሳተፍ/ከባንክ የብድር አገልግሎት ለማግኘት ከሆነ:- እስከ 6 ወር ድረስ፤
- የንግድ ፍቃድ ለማደስ፣ ተሽከርካሪን ለማስፈተሽ (ክላወዶ ለማስደረግ): በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ሒሳባቸውን ለሚዘጉ እስከ ሰኔ 30 እንዲሁም ሒሳባቸውን በራሳቸው የሒሳብ ጊዜ ለሚዘጉ እስከ ሒሳብ ጊዜያቸው ማጠናቀቂያ ቀን ድረስ።
- የንግድ ሥራቸውን በከፊል ወይም በሙሉ ለማቋረጥ፤ የባለቤት ስም ለውጥ ለማድረግ ወይም የንግድ ሃብትን ለማስተላለፍ:- ለ3 ወራት ይሆናል።

## 5.8. የታክስ ክሊራንስ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

- ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ማመልከቻው በቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ የሚሰጥ ሲሆን የማይሰጥ ከሆነ ማመልከቻውን በቀረበ በ14 ቀናት ውስጥ የማይሰጥበትን ምክንያት በጹሑፍ መልስ ይሰጣል፡፡
- የታክስ ክሊራንስ ወረቀቱን ለመስጠት አጠቃላይ/አገልግሎት ኦዲት የሚያስፈልገው ከሆነ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን አንስቶ ባለው በ90 ቀናት ውስጥ ኦዲቱ ተጠናቆ ውጤቱ የሚገለጽለት ስለመሆኑ ለታክስ ከፋዩ በጹሑፍ ያስታውቃል፡፡
- ወረቀት አሰጣጡ ላይ ቅሬታ ያለው ቅሬታውን ለቅ/ጽ/ቤቱ የታክስ ቅሬታ አጣሪ ሥራ ክፍል ማቅረብ ይችላል፡፡

## ❑ ከምዝገባ እና ስረዛ ጋር የተያያዙ ቅጣቶች

- ➢ በታክስ ከፋይነት መመዝገብ ሲገባው ያልተመዘገበ እንደሆነ:- መመዝገብ ከነበረበት ጊዜ ጀምሮ ለምዝገባ እስካመለከተበት ወይም በታክስ አስተዳደሩ አነሳሽነት እስከተመዘገበበት ቀን ድረስ መከፈል ያለበትን ታክስ 25% መቀጮ እንዲከፍል ይደረጋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚከፈል ግብር ከሌለ ለየወሩ 1ሺ ብር ቅጣት ይከፍላል፤



# ቅጣቶች…

- **ሰነዶችን ባለመያዝ የሚጣል ቅጣት**

- መያዝ የሚጠበቅበትን ማንኛውንም ሰነድ ያልያዘ:- ሰነዱ መያዝ በነበረበት የታክስ ዘመን መክፈል ያለበትን ታክስ 20% ቅጣት ይከፍላል፤
- መክፈል የሚኖርበት ታክስ የሌለ እንደሆነ ለገቢ ግብር ሲሆን ብር 20ሺ፤ ለሌላ ታክስ ሲሆን ብር 2ሺ የሂሳብ ሰነድ ላልያዘበት ለእያንዳንዱ የታክስ ዘመን ቅጣት ይከፍላል፤
- ከ2 ዓመት በላይ የሂሳብ ሰነድ ያለመያዝ የንግድ ፈቃድ ስረዛን ያስከትላል።

# ቅጣቶች...

- **በታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር መቅጣት**

I. መለያ ቁጥሩን ሰነድ ላይ ሳይገልጽ የቀረ መለያ ቁጥር ባልተገለጸበት በእያንዳንዱ ሰነድ 3ሺ. ብር ቅጣት ይከፍላል፤

II. TIN አሳልፎ የሰጠም ሆነ የሌላን የተጠቀመ 10ሺ. ብር፤

III. በተራ ቁጥር እና በተጠቀሱት ድርጊቶች ምክንያት ታክስ ከፋዩ ወይም ሌላ ሰው ያገኘው የገንዘብ ጥቅም ከ10ሺ. ብር የሚበልጥ ከሆነ የሚከፍለው የገንዘብ ቅጣት መጠን ካገኘው ጥቅም ጋር እኩል ይሆናል።

# ቅጣቶች…

- ለውጥን ባለማሳወቅ የሚጣሉ ቅጣቶች

- በንግድ ሥራው ላይ ማንኛውንም ለውጥ ያላሳወቀ 2ዐ ሺህ ብር፤
- የመመስረቻ ጽሑፍ/ማሻሻያዎች ያላቀረበ ላላቀረበበት ለእያንዳንዱ ቀን 1ዐሺህ ብር፤_
- ለውጡን በ30 ቀናት ውስጥ ያላሳወቀ፤ የ30 ቀን ጊዜ ገደቡ ካለፈ በኋላ የሚያቀርብ ለዘገየበት ለእያንዳንዱ ቀናት 300 ብር። ይህ ቢኖርም የሚጣለው መቀጫ ከብር 20ሺ ሊበልጥ አይችልም። እነዚህ ቢኖሩም ታክስ ከፋዩ ለውጡን ያላስታወቀው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሆነና ተቀባይነት ካገኘ ይህ መቀጫ ተፈጻሚ አይሆንበትም።

**6.2. የወንጀል ተጠያቂነት**

- ማንኛውም ሰው ከአንድ በላይ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ለመውሰድ የሞከረ፣ የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥሩን ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት የሰጠ ወይም የሌላን ሰው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የተጠቀመ እንደሆነ 20ሺ ብር እና ከ1 እስከ 3 ዓመት በሚደርስ ቀላል እሥራት ይቀጣል።






- ግብር ከፋዩ የሚያከናውናቸውን የአድራሻ ለውጦች ባለማሳወቁ የሚያስከትለውን ቅጣት አብራሩ

## ማጠቃለያ

በዚህ ሥልጠና፤ ስለታክስ ከፋይ ምዝገባ፣ ስለታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ፣ ስረዛ የመረጃ ለውጥ ማሳወቅ እንዲሁም ስለክሊራንስ አሰጣጥ ተዳሰዋል። የቀረቡትን ርዕሰ ጉዳዮች በንግድ ሥራ ዓለም ውስጥ መተግበር ትክክለኛውን የታክስ አስተዳደር ግዴታ በአግባቡና በወቅቱ ለመወጣት ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው። ይህ ካልሆነ ግን የአስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣት ያስከትላል።



## ማጣቀሻ

- የፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008
- የታክስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 407/2009
- ከንግድ አሠራር ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ለውጦች ስለማሳወቅ የወጣ መመሪያ ቁጥር 143/2011
- የታክስ ከፋይ ምዝገባ እና ስረዛ ያፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 3/2011
- የታክስ ክሊራንስ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መ. ቁ.180/2015
- Federal Democratic Republic of Ethiopia Federal Tax Administration Proclamation No. 983/2016 Technical Notes




!

ኢሜይል:-
morethiopia@gmail.com

ዩቲዩብ:-
mor taxpayer education